ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

ማስታወቂያ

ለንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማና የምርጫ መስፈርቶችን ለባለአክሲዮኖች ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ቅዳሜ ህዳር 19 ቀን 2019 ዓ.ም አዲስ አበባ ካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በሚያካሄደው 27ኛ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባንኩን ለቀጣይ ሦስት ዓመታት የሚያስተዳድሩ አስራ ሁለት(12) አባላት የሚኖሩት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫን ያካሄዳል::

በመሆኑም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024፣ SBB/89/2024፣ በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ ፖሊሲ እና አፈፃፀም መመሪያ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በማድረግ በዕለቱ ባለአክሲዮኖች መስፈርቶችን የሚያሟሉ እጩዎችን መጠቆም እና መምረጥ ይችሉ ዘንድ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል::

1. በሁሉም ባለአክሲዮኖች ለሚጠቆሙና ለሚመረጡ እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፣

   1.1. የቦርድ አባላት ምርጫ ከሚደረግበት ቀን አስቀድሞ ቢያንስ ለ2 (ሁለት) ዓመታት የባንኩ ባለአክሲዮን የነበረ/ች፣

   1.2. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ጠንቃቃ እና መልካም ዝና ያለው/ያላት፣

   1.3. የባንኩ ቦርድ አባል ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ/ች እና ኃላፊነቱ/ቷን በአግባቡ ለመወጣት በቂ ጊዜ ያለው/ያላት፣

   1.4. የሌላ ማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ/ች፤

   1.5. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/ች ወይም በተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ የተመረቀ/ች፣

   1.6. በባንኪንግ፣ በፋይናንስ፣ በሪስክ ማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ፣ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ ቢያንስ 7 (ሰባት) ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ላት፣

   1.7. የሌላ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ/ች፤

   1.8. በሌሎች ከአራት በበለጡ ተቋማት ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የማይገኝ/ትገኝ፣

   1.9. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ/ተከሳ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣

   1.10. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ዘችው ድርጅት ወይም ተዕዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት በፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ የዳኝነት ሥልጣን ባለው አካል ወይም በመንግሥት ተቆጣጣሪ አካላት እምነት በመጣስ ጉዳዩች ላይ ተመርምሮ፣ ታግዶ ወይም ተቀጥቶ የማያውቅ/የማታውቅ፣

   1.11. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ዘችው ድርጅት ወይም ተዕዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት የባንክ ወይም የሌላ ብድር ግዴታውን ወይም የታክስ ክፍያውን ባለመክፈል ተከሶ/ሳ ጥፋተኛ ያልተባለ/ች ወይም ንብረቱ/ቷ በሐራጅ ያልተሸጠበት/ባት፣

   1.12. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተዕዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት ሥልጣን ባለው ተቆጣጣሪ የመንግሥት አካል የተጠየቀውን/ችውን መረጃ ያልደበቀ/ች፤ የተሳሳተ የፋይናንስ ወይም ሌሎች መግለጫዎች ያላቀረበ/ች ወይም የተቆጣጣሪ አካላት ውሳኔ ላለመቀበል ወይም ላለመገዛት እምቢተኛ ሆኖ የማያውቅ/የማታውቅ፣

   1.13. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተዕዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የተበላሸ የብድር ታሪክ የሌለው/ላት፣

   1.14. ባለአክሲዮኑ/ኗ አክሲዮን የገዛበትን/ችበትን ገንዘብ ያገኘው/ችው ከከሰረ ሰው ወይም በአስተዳደር ችግር ምክንያት ኪሳራ ካጋጠመው ሰው ያልሆነ ወይም ገንዘቡን ያገኘው/ችው በማጭበርበር ወይም በሕገወጥ መንገድ ያልሆነ፣

   1.15. አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት በቂ ስንቅ ሳይኖረው/ራት ቼክ በመፃፍ የባንክ ሂሳቡ/ቧ ያልተዘጋበት/ባት፣

   1.16. ባለአክሲዮኑ/ኗ የአክሲዮን ባለቤት በሆነ/ች ጊዜ የነበረው/ራት የሀብት መጠን ከአክሲዮኖቹ ዋጋ በላይ የነበረ፣

   1.17. በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ/ሳ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት/ባት የማያውቅ/ታውቅ፣

   1.18. ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቦ/ባ ሲሰራ/ስትሰራ ከኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ/ች፣

   1.19. በራሱ/ሷ ወይም በሚመራው/በምትመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት/ችበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ/ቷ ለዕዳ ማቻቻያነት ያልዋለበት/ባት፣

   1.20. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ንብረቱ/ቷ በሐራጅ ያልተሸጠ፣ ተከሶ/ሳ ያልተፈረደበት/ያልተፈረደባት ወይም እሱ/ሷ የሚመራው/የምትመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት/ችበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን/ችውን ገንዘብ ባለመክፈሉ/ሏ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልገባበት/ባት፣

   1.21. በንግድ ሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡ መመሪያዎች እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተገለፁ ሌሎች መስፈርቶች መሟላት አለባቸው::

ይሠራል ከልብ፣
እንደ ንብ!
Committed to Service Excellence!

2. ገለልተኛ ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በተመለከተ

ገለልተኛ እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሥራ ላይ ባለዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው በአስመራጭ ኮሚቴው አማካይነት ለጉባኤዉ ለምርጫ ይቀርባሉ፡፡ገለልተኛ እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከላይ የተጠቀሱትን አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪነት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

እነዚህም፡-

2.1. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያለው/ያላት እና በባንኪንግ፣በሂሳብ አያያዝ፣ በኦዲት፣ በፋይናንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣በቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ የተመረቀ/ች፣

2.2. በፋይናንስ ሴክተር ውስጥ በመስራት ወይም የፋይናንስ ወይም ኦዲቲንግ ወይም ሪስክ ማኔጅመንት ወይም ተመሳሳይ ዘርፍ በማስተማር ወይም በአማካሪነት ቢያንስ 10 (አስር) ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት፣

2.3. ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ባለአክሲዮን ያልሆኑ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም የባንኩ ሠራተኛ ያልሆኑ ወይም ከእነዚህ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና (ከትዳር አጋር፣ ከልጆች እና ወላጆች ጋር ያለ ዝምድና) የሌለው/የሌላት፣

2.4. ከባንኩ ጋር ማንኛውም ዓይነት የውል ግዴታ ባለው ድርጅት ውስጥ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ያልሆነ/ያልሆነች፣

2.5. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በፍርድ ቤትም ሆነ ከፍርድ ቤት ውጪ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ማንኛውንም ዓይነት የሕግ ክርክሮች በባንኩ ላይ ያላቀረበ/ች፣

2.6. ባለፉት 2 (ሁለት) ዓመታት ውስጥ ከባንኩ ጋር ማንኛውንም የቢዝነስ፣ የንግድ እና ሙያዊ ግንኙነቶችን ያላደረገ/ች፣

2.7. ከብር 50 ሚሊዮን በላይ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት ገንዘብ ነክ የሆነ ኃላፊነት ከባንኩ ጋር ያላቋቋመ/ች እና

2.8. በንግድ ሕጉ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች እና በሌሎች ሕጎች ላይ የተገለፁ ሌሎች መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡፡

3. ማሳሰቢያ

3.1 በባንኩ የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ መሰረት የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር 12 (አስራ ሁለት) ይሆናል፡፡

3.2 አሁን ሥራ ላይ ያለው ቦርድ የእጩ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ ከጉባኤው አስቀድሞ የሚያደርግ ሲሆን የሌሎች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ የሚካሄደዉ እና የሁሉም ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ የሚደረገዉ በባንኩ ባለአክሲዮኖች 27ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ዕለት ማለትም ህዳር 19 ቀን 2019 ዓ.ም ይሆናል፡፡

3.3 በጉባኤው ዕለት የሚመረጠው አምስት አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴ፤ የእጩዎች ዝርዝር በሚከተለው ቅደም ተከተል በ 3 (ሶስት) ምድብ ተቀብሎ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕለቱ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ያስመርጣል፡፡

ሀ) ምድብ አንድ:- ከጠቅላላ የቦርድ አባላት መካከል 1/3ኛ የቦርድ አባላት ተዕዕኖ ፈጣሪ ባለሆኑ ባለአክሲዮኖች ተጠቁመው በእነዚሁ የሚመረጡ፣

ለ) ምድብ ሁለት: ከጠቅላላ የቦርድ አባላት መካከል 1/3ኛ የቦርድ አባላት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ተጠቁመው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ፣

ሐ) ምድብ ሶስት: ከጠቅላላ የቦርድ አባላት መካከል 1/3ኛ የቦርድ አባላት አሁን ሥራ ላይ ባለዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቁመው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች (Independent directors) ናቸው፡፡

3.4 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችሉም፡፡

3.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች የአስመራጭ ኮሚቴው አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፡፡

3.6 አንድ ባለአክሲዮን ራሱን በእጩነት በመጠቆም በምርጫው ላይ መወዳደር ይችላል፡፡

3.7 ሦስት ዓመት ያገለገሉ ነባር የቦርድ አባላት በድጋሚ በእጩነት ከተጠቆሙ መመረጥ ይችላሉ፡፡

3.8 ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ 2 (ሁለት) ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው፡፡

3.9 ከማኅበሩ ጸሐፊ ውጭ 2 (ሁለት) የባንኩ ሠራተኞች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

3.10 የባንኩ ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምፅ መስጠት አይችሉም፡፡

3.11 የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ የሙያና የፆታ ስብጥርን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3.12 አንድ ባለአክሲዮን የሚጠቁመውን እጩ በተመለከተ አጭር ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

3.13 የሚጠቆመው እና የሚመረጠው የቦርድ አባል የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው/የምታገለግለው ሰው ማንነት መታወቅ እና ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ/የምታሟላ መሆን ይኖርበታል/ባታል፡፡

3.14 የምርጫዉ ሂደት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና የምርጫ ፖሊሲ እና አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በማድረግ ይፈፀማል፡፡ የአፈፃፀም መመሪያውን ከባንኩ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የማኅበሩ ጸሐፊ